ለመስማታችን በፊርማችን እናረጋግጣለን የሚል ቢሆንም ኑዛዜው በተናዛዡና በአራቱም ምስክሮች ፊት ስለመነበቡ በግልጽ ያልተገፈ በመሆኑ ኑዛዜው ፈራሽ ነው የሚል ውሣኔ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመስጠቱና ውሣኔውን የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በማጽናቱ የቀረበ አቤቱታ፡፡

**ውሣኔ**

የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠውና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያፀናው ውሣኔ በድምጽ ብልጫ ተሽሯል፡፡

1. ምስክሮቹ በኑዛዜው ላይ ሲናዘዙ ሰምተናል፤ አይተናል ተብሎ የተገለጸው የኑዛዜውን መነበብ የሚያመለክት ነው፡፡
2. ኑዛዜው ተነቧል የሚል ቃል በግልጽ አለመስፈሩ ብቻ ኑዛዜውን በምስክሮቹና በተናዛዥ ፊት አልተነበበም በማለት ኑዛዜውን ፈራሽ ለማድረግ በቂ ምክንያት አይደለም፡፡



የሰ/መ/ቁ. 17429

ጥቅምት 21 ቀን 1998 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

አቶ አብዱልቃድር መሐመድ

አቶ ተገኔ ጌታነህ

ወ/ሮ ሀሣዕና ነጋሽ

ወ/ት ሂሩት መለሰ

**አመልካች፡-** ወ/ሮ ሉሚ ሆርዶፋ - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አቶ ተስፋዬ ከበደ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፈርደናል፡፡

**ፍ ር ድ**

የአሁኗ አመልካች በሥር ፍ/ቤት የሟች ባለቤቴ አቶ ከበደ ዳዲ የኑዛዜ ወራሽ መሆኔ ተረጋግጦ ማስረጃ ይሠጠኝ ብላ አመልክታ ተጠሪ በተቀዋሚነት ቀርቦ በኑዛዜው ላይ ያለው ፊርማ የአባቴ /የሟች/ አይደለም፣ ኑዛዜው እንዲሻር እኔም ሌላ መዝገብ ያስከፈትሁ ስለሆነ መዝገቦቹ በአንድነት ታይተው ይወሰንልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም ሁለቱን መዛግብት መርምሮ በግልፅ የሚደረግ ኑዛዜ በተናዛዡና በአራት ምስክሮች ፊት ካልተነበበ ይህም ሥርዓት መፈፀሙንና የተፃፈበትን ቀን የማያመለክት ካልሆነ ፈራሽ ነው፣ በኑዛዜው ሠነድ ላይ ኑዛዜው በተናዛዡና በአራቱም ምስክሮች ፊት ስለመነበቡ በግልጽ ያልተፃፈ በመሆኑ በፍ/ሕ/ቁ. 881/2/ መሠረት ፈራሽ ነው ሲል ወስኗል፡፡ ከፍተኛ ፍ/ቤት ይህንኑ ውሣኔ አፅንቷል፡፡ አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡

የሰበር አቤቱታው ፍሬ ሃሣብ የኑዛዜው ፅሁፍ መነበቡን ኑዛዜው የሚያሣይ ሆኖ ሣለ ውድቅ መደረጉ ተገቢ አይደለም የሚል ሲሆን፣ ተጠሪ በሥር ፍ/ቤቶች የተፈፀመ የሕግ ስህተት ስለሌለ ፍርዱ ይፅናልኝ ሲል ተከራክሯል፡፡

በዚህ ችሎት ምላሽ ሊያገኝ የሚገባው ነጥብ ኑዛዜው በፍ/ሕ/ቁ. 881/2/ መሠረት የተደረገ አይደለም መባሉ ተገቢ መሆን ያለመሆኑ ነው፡፡

ጳጉሜ 5 ቀን 1990 ዓ.ም. በተፃፈው የአቶ ከበደ ዳዲ ኑዛዜ ላይ የኑዛዜው ዝርዝርና የአራት ሽማግሌዎች /ምስክሮች/ ስም ከተፃፈ በኋላ



#እኛ ከዚህ በላይ ስማችን የተጠቀሰው ሽማግሌዎች በትክክለኛ አዕምሮዋቸው ሆነው ሲናዘዙ ሰምተናል፤አይተናል; ተብሎ ተጠቅሷል፡፡ ከተናዛዡና ከአራቱ ምስክሮች ፊርማ ቀጥሎ ደግሞ #ይህንኑ ቃል ለመስማታችን በፊርማችን እናረጋግጣለን ; ይላል፡፡

የፍ/ሕ/ቁ.881/2/ #ኑዛዜው በተናዛዡና አራት ምስክሮች ፊት ካልተነበበና ይኸም ሥርዓት /ፎርማሊቲ/ መፈፀሙንና የተፃፈበትንም ቀን የሚያመለክት ካልሆነ በቀር ፈራሽ ነው; በማለት ሲደነግግ የፍ/ሕግ ቁጥር 881/3/ ደግሞ #ተናዛዡና ምስክሮቹ በኑዛዜው ላይ ወዲያውኑ ፊርማቸውን ወይም የአውራ ጣት ምልክታቸውን ካላደረጉበት በቀር ፈራሽ ነው; ይላል፡፡

እነዚህ ሁለት ንዑሳን አንቀጾች አንድ ኑዛዜ አራት ነገሮችን ማለትም ኑዛዜው የተደረገበትን ቀን፣ በአራት ምስክሮች ፊት መደረጉን፣ ኑዛዜው በተናዛቹና በምስክሮች መፈረሙንና መነበቡን ማሣየት እንዳለበት ይደነግጋሉ፤ ከፍ ሲል ከኑዛዜው ፅሁፍ ላይ ወስደን ካሠፈርነው መረዳት የተቻለው ኑዛዜው ጳጉሜ 3 ቀን 1990 በሚል ቀን የተፃፈበት፣ የአራት ምስክሮች ስም ያለበት፣ ምስክሮቹና ተናዛዡ

የፈረሙበት መሆኑን ነው። ከዚህ ሌላም በኑዛዜው ላይ #ሲናዘዙ ሠምተናል፣ አይተናል; ተብሎ መገለፁም የኑዛዜውን መነበብ የሚያመለክት ነው። ሕጉ የኑዛዜውን መነበብ አስፈላጊነት ያስቀመጠው በሚነበብበት ወቅት ሟች/ተናዛዥ የተናገረው በትክክል በፅሁፍ መስፈሩን እንዲረዳና የተናዛዡ ፈቃድ መሟላቱን ማረጋገጥ እንዲቻል ነው። ከላይ በተጠቀሰው የኑዛዜው ክፍል #ሲናዘዙ ሠምተናል፣ አይተናል; በሚል የሠፈረው ምስክሮች ያዩትና የሰሙት ኑዛዜው ሲደረግና የተፃፈው ኑዛዜ ሲነበብ ነው ተብሎ መገመት ይኖርበታል።

የሥር ፍ/ቤቶች ኑዛዜውን ለማፍረስ የሚያበቃ የሕግ መሠረት በሌለበት በኑዛዜው ፅሁፍ ላይ ኑዛዜው #ተነቧል; የሚል ቃል ባለመኖሩ ብቻ ኑዛዜው በምስክሮችና በተናዛዡ ፊት ስለመነበቡ አልተፃፈም በማለት ፈራሽ ማድረጋቸው ተገቢ ሆኖ አልተገኘም።

## ው ሣ ኔ

የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 71/93፣ እንዲሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ.03644 የሠጧቸው ውሣኔዎች ተሽረዋል።



ኑዛዜው በፍ/ሕ/ቁ. 881 በተደነገገው መሠረት የተከናወነ በመሆኑ የፀና ነው ብለናል፤ ይፃፍ፤ መዝገቡ ተዘግቷል።



## የሃሳብ ልዩነት

ስሜ በተራ ቁጥር አራት የተጠቀሰው ዳኛ አብዛኛው ድምፅ የኑዛዜውን ሕጋዊነት በማረጋገጥ በሰጠው ውሣኔ የማልስማማ በመሆኑ የሃሳብ ልዩነቴን እንደሚከተለው አሰፍራለሁ።

ከሦስቱ ዓይነት ኑዛዜዎች አንዱ በግልፅ የሚደረግ ኑዛዜ ነው። /የፍ/ብ/ሕግ/ቁ. 880/ሀ/። ይህ አይነት ኑዛዜ ለማፅናት በተናዛዡና በአራት ምስክሮች ፊት መነበብና ይኸም ስርዓት መፈፀምን ማመልከት ይኖርበታል። /የፍ/ብ/ሕግ/ቁ. 881/2/። ኑዛዜ የሟቹ ጥብቅ የሆነ ራሱ የሚፈፅመው ሥራ ነው። /የፍ/ብ/ሕግ/ቁ. 857/1/ የማንበብ ሥርዓት አስፈላጊ የሆነው በግልፅ የሚደረግ ኑዛዜ ተናዛዡ እየተናገረ ማናቸውም ሌላ ሰው ሊፅፈው ስለሚችል በሌላ ሰው የተፃፈው ቃል በትክክል የሟች ቃል መሆኑን ለማረጋገጥ ነው። ምስክሮቹ ኑዛዜ የተፃፈበትን ቋንቋ ለማወቅና የተፃፈውን ለመስማት ወይም ለማንበብ ራሳቸው ችሎታ ያላቸው መሆንም አለባቸው። /የፍ/ብ/ሕግቁ.837/

ይህም ድንጋጌ በግልጽ በሚደረግ ኑዛዜ የመነበብ ስርዓት አስፈላጊና መነበቡም በትክክል በማያጠራጥር ሁኔታ መፈፀም ያለበት መሆኑን ያመላክታል፡፡

ወደ ጉዳዩ ስንመጣ አብዛኛው ድምፅ ኑዛዜው ተነቧል የሚል መደምደሚያ ላይ የደረሰው የአቶ ከበደ ኑዛዜ የአራቱን ምስክሮች ስም ከጠቀሰ በኂላ #ሲናዘዝ ሰምተናል አይተናል; እንዲሁም ከተናዛዡና ከምስክሮች ፊርማ ቀጥሎ ደግሞ ይህንኑ ቃል ለመሰማታችን #በፊርማችን እናረጋግጣለን; የሚሉ ቃላቶች በመስፈራቸው ነው፡፡ በእኔ እምነት ምስክሮቹ ሰምተናል አይተናል የሚሉት ሟች ኑዛዜውን በመስጠት ላይ እያለ የተናገረውን ሊሆን ስለሚችል እነዚህ ቃላቶች በርግጠኝነት መነበብን አያመለክቱም ከነዚህ ቃላቶች ሕጉ እንዲፈፀም የሚፈለገውን የማንበብ ሥርዓት መፈፀም አለመፈፀም በትክክል ማረጋገጥ አይቻልም፡፡ ተፈፅሟል ለማለትም ያዳግታል፡፡ ይህ ሕጉ በግልፅ እንዲፈፀም የሚፈልገው ስርዓት መፈፀም ሳይረጋገጥ ደግሞ ኑዛዜው ሊፀና አይገባም፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤቶች ውሣኔ የሚሽርበት ምክንያት ስለሌለ ሊፀና ይገባል ስል በሀሳብ ተለይቻለሁ፡፡



የሰበር መ/ቁ. 17533

ጥቅምት 18 ቀን 1998

ዳኞች፡ - 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

2. አቶ አብዱልቃድር መሐመድ

3. አቶ ሐጐስ ወልዱ

4. አቶ ዳኜ መላኩ

5. አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ

**አመልካች፡** - የኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለሥልጣን

**መልስ ሰጪ፡** - አቶ ሙሉ አብርሃ

*ስለዲክራሲዮን አሰጣጥ - የመጋዘን ኪራይ ስለሚታሰብበት ጊዜ፡ -*

*የጉምሩክ ባለስልጣን እንደገና ለማቋቋምና አሠራሩን ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር 60/1989 ዓ.ም.፣ አንቀጽ 2/18/፣ 43/1/ /ሀ/*

አመልካች ከውጭ ያስመጣሁትን እቃ የጉምሩክ ስርአት አልተፈጸመበትም በሚል በመጋዘን በማቆየት ያስከፈለኝን የመጋዘን ኪራይ እና ዲክላራሲዮን ባለመስጠቱ እቃውን ለመሸጥ እንዳይቻል በማድረግ በመጋዘን በማስቀመጥ ለኪራይ እንዳወጣ ያደረገኝን ወጪ እንዲተካልኝ በማለት መ/ሰጪ ያቀረቡትን ክስ በመቀበል መ/ሰጪ በጠየቁት ውሳኔ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በማጽናቱ የቀረበ አቤቱታ